www.abyssinialaw.com



9ኛ ዓመት ቁጥር 24
9th Year № 24

ባህር ዳር ሰኔ 28 ቀን 1996 ዓ.ም
Bahir Dar July 5,2004

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

# ዝክረ-ሕግ
# ZIKRE HIG

## OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA


| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር 4·25<br>Price | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | ፖ.ሣ.ቁ 312<br>B.O.BOX |


| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| ደንብ ቁጥር 14/1995 ዓ.ም | Regulation No. 14/2003 |
| በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጥብቅና ሙያ ፈተና፣ ፈቃድ አሰጣጥና ድርጅት ምዝገባ ክፍያዎች መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | The Amhara National Regional State Advocacy examination, liesencing and fixing of legal firm registration fees, Council of the Regional Government Regulation. |

ደንብ ቁጥር 14/1995 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጥብቅና ሙያ ፈተና፣ ፈቃድ አሰጣጥና ድርጅት ምዝገባ ክፍያዎችን ለመወሰን የወጣ የክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ

በአማራ ብሔራዊ ክልል ፍ/ቤቶች በሚታዩ የክልል ጉዳዮች ላይ የጥብቅና አገልግሎት ለሚሰጡ ጠበቆች

Regulation No. 14/2003

A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE DETERMINATION OF FEES OF ADVOCACY EXAMINATION, LICENSING AND LEGAL FIRMS REGISTRATION IN THE AMHARAR NATIONAL REGIONAL STATE

Whereas, it is found necessary to fix the service fees required from those advocates who provide

www.abyssinialaw.com



ፈተና ለመውሰድ፣ የሙያ ሥራ ፈቃድ ለማግኘትና ለማሣደስ እንዲሁም የጥብቅናና የህግ ምክር አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ለማስመዝገብ የሚፈለገውን የአገልግሎት ክፍያ መወሰን በማስፈለጉ፣

advocacy service pertaining to cases of regional nature entertained by the courts of Amhara National Region so as to take the advocacy license examinations prepared by the Regional Justice Bureau; obtain and get renewed advocacy license as well as have registered the advocacy and legal counseling service providing firms thereof;

በብሔራዊ ክልሉ የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ፣ ምዝገባና የጠበቆች ሥነ ምግባር መቆጣጠሪያ አዋጅ ቁጥር 75/1994 ዓ.ም. አንቀጽ 62 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር እንደተደነገገው አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በክልሉ ውስጥ የፌዴራሉንም ሆነ የክልሉን መንግስታት አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ ይዘው የዘመኑን የሥራ ግብር እየከፈሉ የጥብቅና ሙያ አገልገሎት በመስጠት ላይ የነበሩት ጠበቆች ከደንበኞቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ይቻላቸው ዘንድ ለያዙት የጥብቅና ፈቃድ ያለ ፈተና በክልሉ ፍትሕ ቢሮ በኩል እውቅና የሚሰጥበትን ሁኔታ ማመቻቸት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

Whereas, as provided for under article 62 sub article 1 of the licensing, registration and advocates' code of conduct controlling proclamation No. 75/2002 of the National Regional State, it is found appropriate, for those advocates who used to render advocacy service in the Region by holding the federal or regional state's first and second grade advocacy license against paying the annual tax prior to the enactment of the proclamation, to facilitate conditions whereby recognition of the advocacy license they already had may be availed with out examination by the Regional Justice Bureau with the view to enabling them make advocate-client relationship continuous;

የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና በአብክመ የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ፣ምዝገባና የጠበቆች ሥነ ምግባር መቆጣጠሪያ አዋጅ ቁጥር 75/1994 ዓ.ም. አንቀጽ 63 ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

Now, therefore, the council of the Amhara National Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provisions of Article 58, Sub article 7 of the revised Regional constitution and Article 63 of the Amhara National Regional State's advocacy licensing, registration and advocates code of conduct controlling proclamation No.75/ 2002, hereby issues this regulation.

www.abyssinialaw.com



# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ " የጥብቅና ሙያ ፈተና፣ ፈቃድ አሰጣጥና ድርጅት ምዝገባ ክፍያዎች መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 14/1995 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ :-

1. "አዋጅ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጥብቅና ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ፣ ምዝገባና የጠበቆች ሥነ ምግባር መቆጣጠሪያ አዋጅ ቁጥር 75/1994 ዓ.ም. ነው::
2. "ጠበቃ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 3 ስር ትርጓሜ የተሰጠው የህግ ባለሙያ ነው::

## 3. የደንቡ ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በአማራ ብሔራዊ ክልል በየትኛውም ደረጃ በሚገኙ መደበኛ ፍ/ቤቶች ወይም ሌሎች የዳኝነት አካላት የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለማበርከት የክልሉ የጥብቅና ሙያ ፈቃድ እንዲሰጣቸው በሚያመለክቱ ጠበቆች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል::

# PART ONE

# GENERAL PROVISIONS

## 1. Short Title

This regulation may be cited as " fixing fees for the provision of advocacy examination, licensing and legal firms registration, Council of the Regional Government regulation No.14/2003."

## 2. Definitions

Unless the context other wise requires, in this regulation:

1. "Proclamation" means the advocacy licensing, registration and advocates' code of conduct controlling proclamation No. 75/2003 of the Amhara National Regional State.
2. "Advocate" means a lawyer defined under article 2 sub-article 3 of the proclamation.

## 3. Scope of application

This regulation shall be applicable on all advocates who seek for the regional advocacy license so as to render advocacy services before Regular Courts or other Quasi-judicial organs at any level in the Amhara National Region.

opra operate

www.abyssinialaw.com



# ክፍል ሁለት
# የጥብቅና ሙያ ፈተናና ፈቃድ ክፍያ

## 4. የጥብቅና ሙያ ፈተና ምዝገባ

1. በአዋጁ አንቀጽ 10 መሰረት የጥብቅና ሙያ ፈተና እንዲሰጠው የሚያመለክት ማንኛውም ጠበቃ በደረጃው የሚሰጠውን ፈተና ለመውሰድ በክልሉ ፍትሕ ቢሮ በሚወጣ ማስታወቂያ መሰረት መመዝገብ አለበት::
2. በማስታወቂያው መሰረት ለአንደኛ ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ ለፈተና የሚመዘገብ ጠበቃ ብር 200/ሁለት መቶ ብር/ የሚከፍል ሲሆን ለሁለተኛ ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ ፈተና የሚመዘገብ ብር 150/አንድ መቶ ሃምሣ ብር/ይከፍላል::
3. ክፍያው ለአንድ ፈተና ብቻ የሚያገለግል ይሆናል::

## 5. ስለጥብቅና ፈቃድ ማውጫ፣ ማሣደሻና መተኪያ ክፍያ

1. በአዋጁ አንቀጽ 8 ወይም 9 ላይ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች ያሟላ ማንኛውም ጠበቃ ሁለተኛ ወይም አንደኛ ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ እንዲሰጠው ለክልሉ ፍትህ ቢሮ ያመለክታል::

# PART TWO
# ADVOCAY EXAMINATION AND LICENCEING FEES

## 4. Registration for Advocacy Examination

1. In accordance with Art.10 of the proclamation, any advocate who may apply to be provided with the advocacy examination set for the grade shall be registered pursuant to the notice to be issued by the Regional Justice Bureau.
2. The advocates to be registered according to the notice for the examination of first grade advocacy license shall pay birr 200 (two hundred birr) and the one who would be registered for the second advocacy license shall pay birr 150 (one hundred fifty birr).
4. The payment shall serve only for one examination.

## 5. Fees for Acquisition, Renewal and Substitution of Advocacy License.

1. Any advocate who fulfills the requirements under Art. 8 or Art. 9 of the proclamation may apply to the Regional Justice Bureau to acquire first or second grade advocacy license.

licence

www.abyssinialaw.com



2. ማመልከቻው በጥብቅና ፈቃድ ገምጋሚና የጠበቆች የችሎታ ብቃት መለኪያ ቦርድ ታይቶ ፈቃዱ እንዲሰጠው የተወሰነለት ጠበቃ ፈቃዱን ሲወስድ 400 ብር/ አራት መቶ ብር/ መክፈል ይኖርበታል::

3. ማንኛውም ጠበቃ ፈቃዱን ለማሣደስ ብር 300 /ሶስት መቶ ብር/ ይከፍላል::

4. ፈቃዱ የተበላሸበት ወይም የጠፋበት ጠበቃ በምትኩ ፈቃድ ማግኘት የሚችል ሲሆን ለፈቃዱ መተኪያ ብር 350 /ሶስት መቶ ሃምሣ ብር/ መክፈል ይኖርበታል::

5. ሁለተኛ ደረጃ የጥብቅና ሙያ ፈቃድ ይዞ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ሲሰጥ የነበረ ጠበቃ አንደኛ ደረጃ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ እንዲሰጠው ሲጠይቅ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2፣ 3፣ እና 4 ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ::

2. Any advocate whose application is considered by the license evaluating and advocates capacity assessment board and is allowed to take the license shall pay birr 400 (four hundred birr).

3. Any advocate shall pay birr 300 (three hundred birr) to have renewed his license.

4. Any advocate whose license has been damaged or lost may get the substitute against paying birr 350 (three hundred fifty birr).

6. Where any advocate who was rendering advocacy services using the second grade advocacy license seeks for the first grade advocacy license, the provisions of sub Arts. 1, 2, 3 and 4 of this article shall apply.

## 6. ስለጥብቅና አገልግሎት ድርጅት ምዝገባ ክፍያ

1. በክልሉ ውስጥ የጥብቅና ሙያ ወይም የህግ ምክር አገልግሎት መስጫ ድርጅት የሚያቋቁም ማንኛውም ጠበቃ ድርጅቱን ለክልሉ ፍትህ ቢሮ ማስመዝገብ አለበት::
2. ድርጅቱን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚያስመዘግብ ጠበቃ ለሚያገኘው የምዝገባ አገልግሎት ብር 450 / አራት መቶ ሃምሣ ብር/ ይከፍላል::
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት ድርጅቱን ያስመዘገበ ማንኛውም ጠበቃ ፈቃዱን ለማሣደስ ብር 350/ ሶስት መቶ ሃምሣ ብር/ ይከፍላል::

## 6. Fees for the Registration of Legal Firms

1. Any advocate who establishes legal advocacy or counseling service firms in the Region shall have his firms registered by the Regional Justice Bureau.
2. The advocate who has his firm registered in accordance with Sub art. 1 of this Article hereof, shall pay birr 450 (four hundred fifty birr) for the registration service he has obtained.
4. Any advocate who has his firm registered pursuant to sub arts. 1 and 2 of this article, shall pay birr 350 (three hundred fifty birr) for the renewal of same.

www.abyssinialaw.com



# ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 7. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት የፌዴራል መንግስቱን ወይም የክልሉን የጥብቅና ሙያ ፈቃድ ይዘው በክልሉ ፍ/ቤቶች የጥብቅና ሙያ ግልጋሎት ሲሰጡ የነበሩ ጠበቆች የክልሉ የጥብቅና ፈቃድ እንዲሰጣቸው በአዋጁ አንቀጽ 62 ንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ከጠየቁ ያለ ፈተና በያዙት የጥብቅና ሙያ ተገቢው ፈቃድ ይሰጣቸዋል።
2. የዚህ ደንብ አንቀጽ 4 እና 5 ድንጋጌዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ፈቃድ በሚሰጣቸው ጠበቆች ላይም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

### 8. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፍትሕ ቢሮ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

### 9. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
ሰኔ 28 ቀን 1996 ዓ.ም
ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ርዕሰ መስተዳድር

# PART THREE

## MISELLANEOUS PROVISIONS

### 7. Transitory Provisions

1. Advocates who were practicing before the Regional Courts carrying the Federal or Regional State's advocacy license prior to the issuance of the proclamation shall be provided with the appropriate license of the same grade without examination provided that they apply for it within the time stipulated under Art. 62 Sub art. 2 of the proclamation.
2. The provisions of Arts. 4 and 5 of this regulation shall as well apply on advocates to be licensed pursuant to sub-Art. 1 of this article hereof.

### 8. Power to Issue Directives

The Amhara National Regional State Justice Bureau may issue directives necessary for the implementation of this regulation.

### 9. Effective Date

This regulation shall enter in to force as of the date of its publication in the Ziker Hig Gazette of the Regional State.

**Done at Bahir Dar**
**This 5 th Day of July, 2004**
**YOSEF RETA**
**Head of Government of the Amhaara National Regional State**

www.abyssinialaw.com

www.abyssinialaw.com

www.abyssinialaw.com

www.abyssinialaw.com